ከመስፍን፡ወልደ፡ማርያም።

እ ን ጉ ር ጉ ሮ

ከመስፍን ወልደ ማርያም

የደራሲው መብት
በሕግ የተጠበቀ ነው ።

መስከረም ፲፱፻፹፯ ዓ ፡ ም ፡
በኮከብ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ማ ው ጫ

ገጽ

መ ቅ ድ ም

፩/ ግድ የለም ሰምታለች ፩—፫
፪/ ታሪክ ፬
፫/ ተጠየቅ መስከረም ፭—፯
፬/ የሰው አውራ ፰
፭/ የቁልቁለቱ ኃይል ፱
፮/ ሰው አልተፈጠረም ፲
፯/ የወፍጮ እንጉርጉሮ ፲፩—፲፪
፰/ ማኅበር ፲፫—፲፬
፱/ ቻይ መሬት ፲፭
፲/ የገበሬ እንጉርጉሮ ፲፮
፲፩/ ኧረ ስማ እግዚአብሔር ፲፯—፲፰
፲፪/ እነዚያ ጆስት ወጣት ፲፱—፳
፲፫/ እንዴያ ዝም ፳፩—፳፪
፲፬/ -ወይ እንገላገል ፳፫
፲፭/ ብቸኝነት ፳፬—፳፭
፲፮/ መሰላል መውጣት ፳፮

		ገጽ
፲፯/	ቆሜ እየዋለሁ	፳፯—፳፰
፲፰/	የት አለ ወንዱ ልጅ?	፳፱
፲፱/	ግራ ገባኝ	፴
፳/	ሞት ማለት	፴፩—፴፫
፳፩/	በጋን ያለ መብራት	፴፬
፳፪/	የሞተ ኅሊና	፴፭
፳፫/	ምጽዓት	፴፮—፴፯
፳፬/	ስብሐት ለጨለማ	፴፰—፴፱
፳፭/	የጥንቱ አገረሸ-	፵
፳፮/	ናፍቆት	፵፩
፳፯/	ከልቤም አትወጪ!	፵፪
፳፰/	ፍቅር መስዋዕት ሆነ	፵፫
፳፱/	የኔ ፍቅር	፵፬
፴/	የሕይወት ቃር	፵፭
፴፩/	እኔ በአንቺ አልፈርድም	፵፮
፴፪/	ዕፀ በለስ	፵፯—፵፱
፴፫/	እስናቆች	፶
፴፬/	ባልተመቸ ጊዜ	፶፩—፶፪
፴፭/	ይናፍቀኛል	፶፫
፴፮/	ሕያው ኢትዮጵያ	፶፬—፶፮

መቅድም ፤

ሰው ሁልጊዜም ጊዜውና ሁኔታው በሚያጋጥመው ወይም ከውስጡ በሚመነጨው የሕይወት ኃይል ስሜቱ በጣም ይለዋወጣል ። ሐዘንና ደስታ ፤ ልቅሶና ሳቅ ፤ ትዝታና ተስፋ ፤ ጥርጣሬና እምነት ፤ ጥላቻና ፍቅር ፤ ስቀቀንና እለኝታ ወዘተ ይፈራረቁበታል ። የሕይወት ጣዕሙ የሚታወቀውም በዚህ ዓይነቱ የስሜት መፈራረቅ ነው ይባላል ። አንድ ስሜት ብቻ ሕይወቱን ቀስፎ የያዘው ሰው የሕይወትን የተለያየ መልክ ለማየት አይችልም ፤ ለመማር አይችልም ፤ መንፈሱም ሊበለጽግ አይችልም ።

ከራሱ ውጭ የሚያጋጥመውም ሆነ ከውስጡ የሚመነጨው ኃይል ግጭትን ወይም ትግልን ያስከትላሉ ። ያን ጊዜ ነው ግራ የሚገባው ፤ ያን ጊዜ ነው በመንታ መንገድ ላይ ልብ የሚሰቀለው ፤ ያን ጊዜ ነው የዓለም ስፋትና የጊዜ ዘለዓለማዊነት ሰውንና ሕይወቱን ኢምንት ቅጽበት የሚያደርጉት ፤ ያንጊዜ ነው የኑሮ ውጥንቅጥና የሰው የምኞት ባርነት ጎልቶ የሚታየው ። የተመኙት ሲገኝ ሌላ ምኞት ይተካል ። ምኞት ያነሣል ፤ ምኞት ይጥላል ። መውደቅም ሆነ መነሣት የሕያውነት ምልክቶች ናቸው ። ወድቆም ሆነ ቆሞ መቅረት ደግሞ የበድንነት ምልክቶች ናቸው ። ሕይወት ያለው ሰው ከውስጥ ከራሱ ከሚልቁ ልዩ ልዩ ስሜቶች ጋር ፤ ከውጭም ከሌሎች ስሜቶች ጋር ሁልጊዜ ይታገላል ።

አንድ ሰው ደስ ብሎት ሲስቅና ሲፈነድቅ ነገሩም ባይገባን አብረን እንስቃለን ። አንድ ሰው ከፍቶት ሲያለቅስ ነገሩም ባይገባንና ባናለቅስም ይከፋናል ። ስሜት ያለቋንቋ ይተላለፋል ማለት ነው ። ይህንን ያለቋንቋም እንኳን የሚተላለፈውን ስሜት በልዩ ልዩ ዘዴ (በቃላት ፤ በቀለም ፤ ወይም በዜማ ውበት) የሚያስተላልፉ ሰዎች አሉ ።

ግጥም መግጠም ፤ ከፍ ሲልም ቅኔ መቀኘት የባለሙያዎች ሥራ ነው ። የእነዚህን ባለሙያዎች የቃላት አመራረጥ ፤ የቃላት አሰካክና የዜማቸውንም ስልት አድናቂ ነኝ ። በተሰጥዎም ሆነ በትምህርት በዚህ የሙያ ዓለም ያለሁ ለማስመሰል ፍላጎት የለኝም ።

ክራር ወይም መሰንቆ ወይም በገና መምታት ወይም ዋሽንት መንፋት የሚችሉ ሰዎች የታደሉ ናቸው ። ስሜታቸውን የሚያሰሙና የሚያስተጋቡ መሣሪያዎች አሉአቸው ። በቧምቧ ውስጥ ተመርቶ እንደሚፈስ ውሀ ስሜታቸው በእጃቸው አልፎ መሣሪያቸውን ሲያናግረው መልሰው ይሰሙታል ። ከውስጥ የሚያስጨንቀው ስሜት ጣዕምና ለዛ አግኝቶ ፤ ለስልሶና ተራቆ ሌላ ሆኖ አስጨናቂነቱን ትቶ ይመለሳል ። ያን ጊዜ መንፈስ መዝናናት ይጀምራል ። ሳስበው እንዲህ ይመስለኛል ። የሆነ ሆኖ ይኸም እኔ የሌለኝ ችሎታ ነው ።

ጥሩ ድምፅ ያላቸው ሰዎች በድምፃቸው ውበት ቃል አልቦ በሆነ ዜማ ጭምር ስሜታቸውን ይገልጹታል ፤ ይወጣላቸዋል ። ይኸም ችሎታ የለኝም ።

የእኔ ተራ እንጉርጉሮ ነው ፤ የባለሙያ ድርሰት አይደለም ። እንጉርጉሮ ሐዘን ፤ ትዝታ ፤ ቅሬታ ፤ ትካዜ ፤ የሚያቀጣጥሉትን የስሜት ነበልባል መቀነሻ ዘዴ ነው ። እንጉርጉሮ የስሜትን ነበልባል ወደውጭ በመምራት የነፍስን ጭንቀት ይቀንሳል ብዬ አምናለሁ ። የአእምሮ ሚዛን እንዳይዛባ ፤ ቆሽት እንዳይደብን ፤ እንጀት እንዳያር ፤ ሆድ እንዳይቆስል እንጉርጉሮ ዋና መከላከያ ሳይሆን አይቀርም ። አንድ ስሜት ነፍስን ወጥሮ ሲይዝና ችኮ መንቻካ ሆኖ ሌላ ስሜት ወይም ሌላ ሀሳብ አላስገባ ብሎ ልብንና አእምሮን ሲያፍን እንጉርጉሮ ወደር የሌለው ፈውስ ነው ። ድብን ብሎ ከነፍስ ጋር የተቋጠረውን ስሜት እንጉርጉሮ ይፈታዋል ።

ሥርዓትን እንዲይዝና በተጠረገለት መንገድ እንዲሄድ ከተደረገ ስሜት ሕይወትን ያበለጽጋል ። እንዲያውም የሚያበረክተው የመንፈስ ብልጽግና በስሜቱ ጽናትና ኃይል መጠን ነው ለማለት ይቻላል ። የበረታ ስሜት የበለጠ ያበለጽጋል ማለት ነው ። ያበለጽጋል ስል ያስተምራል ፤ ራስንም ሆነ ሌሎችን በትክክል ለመመዘን ይረዳል ማለቴ ነው ። እለዚያ ስሜት ራስንም ፤ ሌሎችንም ወደጉዳትና ወደ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል ኃይል ነው ።

እንጉርጉሮ በመሠረቱ የግል ነው ፤ ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ የተዘጋጀ አይደለም ማለት ነው ። አንድ ሰው ከገዛ ራሱ ስሜት ጋር የሚያደርገው ትግል ነው ። ራሱ፤ራቁቱን እውነቱንየሚያይበትመስተዋትነው።ቢሆንም የሰው ሁሉ መሠረታዊ ስሜት አንድ ዓይነት በመሆኑ ተመሳሳይ አጋጣሚም ተመሳሳይ ስሜትን ሊፈጥር ይች ላል ። ከዚያም በቀር አንድ ሰው የጠቅላላው ኅብረተ ሰብ ደስታና ምኞት ፤ ስቃይና ጭንቀት ፤ ተስፋና ምኞት ተካፋይ መሆኑ በጥልቅ ከተሰማው በኢምንትና የግል በሆነ መንገድ ያንን ጥልቅ ስሜት እንደኅብረተሰቡ ሆኖ ሊያስተጋባ ይችላል ። የእኔ ሙከራ ተሳክቶ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መፍረዱ የአንባቢዎች ፋንታ ነው ።

ይህ እንጉርጉሮ በአለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ በየ ጊዜው የተጻፈ ነው ። ዕድል በተገኘ ጊዜ አንዳንዶቹ በአ ለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ በጋዜጣዎች ወይም በመጽ ሔቶች ውስጥ እየታተሙ ወጥተዋል ። እነዚህን በዚህ (*) ዓይነት ምልክት ለመለየት ይቻላል ። አብዛኞዎቹ ግን ታትመውም አያውቁም ።

— ግድየለም ሰምታለች — (*)

ባል ያላገኘች ሚስት ፤
ያልወለደች እናት ፤
እግዜር ደስ ያለው ለት ፤
ያለ እንከን የሠራት ፤
መልኬ በቃኝ ብላ ዓለምን የናቀች ፤
እንዲት ሴት ነበረች ።
ዝም ልል አልቻልሁም ፤
የልቤን ነገርሁአት ፤ ብትወድም ባትወድም ።
«አንቺ ሴት አንቺ ቆንጆ
ለምን ትኖሪአለሽ በዚች ትንሽ ጎጆ?
በባሕር ማዶ ጡብ ቤት መሥራት ሲቻልሽ ፤
ደሳሳዋን ጎጆ ምን ዕድል አስመኘሽ?
እስከመቼ ድረስ ትከናነቢያለሽ?
እስከመቼ ድረስ ትሽኮረመሚያለሽ?
መስተዋት ግገርና መልክሽን እወቂው ፤
ጉድለትሽ ምንድን ነው? ውበትሽስ የት ነው?
በመጉሳቆልሽ ማን ነው የሚጎዳው?
ማንስ ነው የሚያዝነው?

ጠይቂ ፣ መርምሪ ፣ ተረጂው እውነቱን ፣
ራስሽ ለራስሽ አስተካክዪው ፍርዱን ፣
ሐዘን ነው ስንፍና? ወይስ ድንቁርና?
የሚያኮራምትሽ በዓለም በጤና!
በቅናት ሲያሽካኩ ጎረቤቶች ሁሉ ፣
እንብለጥ ፣ እንብለጥ ፣ እየተባባሉ ፣
ካቅማቸው ፉንንቱ ሲመጣደቁብሽ!
ማን ይድላው ብለሽ ነው አንቺ እንዲህ መሆንሽ?
ማጥንሽን ከፊቺው ፣
ጌጥሽን እስቲ አውጪው ፣
ይውረድ ክንብንብሽ ፣
ቀና በይ ካንገትሽ!
ተራመጂ በምነት ፣
ኩሪ ባለሽ ውበት!

አፈስ ፣ አፈስ አርጊው ፣ አርምጃሽ ይጣደፍ ፣
በድን አትምሰዪ ፣ ይቅርብሽ መንከርፈፍ!

ቀሚሶች አሠሪ ሰፋ አርጊው ጥበቡን
ጸጉርሽም ይበጠር ተዪው ክንብንቡን ።

ቤትሽንም አጽጂው ተባዮቹ ይጥፉ ፣
ምሰሶው ይቃና ይጠረግ ምድራፉ ።

እረ ምን ጎደለሽ? ካካል ፣ ከአእምሮሽ?
ለጋ ነሽ ፣ መልካም ነሽ ፣ ሙሉ ነሽ ፣ ትርፍ ነሽ ።
ሕይወት ያለተስፋ ኩራትስ ያለክብር ፣
ወግ ያለማዕረግ ፣ ምኞትስ ያለግብር ፣
ከንቱ ነው ፣ መና ነው ፣ ሕልም ነው እወቂው ፣
መካንነት መርጠሽ ዘር ልታጠፊ ነው።
ለሥጋ ነው? ለነፍስ?
ሕያው ለሙት መፍረስ!
ጤንነት ነው? እብደት?
ሕይወትን መሠዋት!
በትካዜ ፈዝዛ ዓይን ዓይኔን እያየች ፣
ሳወርደው መዓቱን ጭጭ ብላ አዳመጠች ።
ነግሬአት ፣ ነግሬአት ፣ አተኩራ እያየች ፣
«አዬ የልጅ ነገር!» ብላ ጥላኝ ሄደች ።
ትካዜ ፣ ሐዘንዋን ፣ ጭንቅና ሥቃይዋን ፣
አጋብታብኝ ሄደች ፣ ቀረሁኝ ብቻዬን ።
ሀሳቤን ጠልታ ነው? ወይስ ልጅነቴን?
ሳልጠይቃት ሄደች ፣
ግድ የለም ስምታለች ፣
ግድ የለም ስምታለች ።

ታሪክ (*)

ያለፈው አለፈ ፣
ሄደ እየከነፈ ።
ይረሳ ፣ አይወሳ ፣
ትናንትና ሬሣ !
ከራስ በላይ ነፋስ ! ስንኩል ፍልስፍና ፣
ደካማ አእምሮና ደካማ ሕሊና ፣
መሆኑን አያውቁም ዛሬ ትናንትና ።
ትናንት መሠረት ነው ዛሬ የቆመበት ፣
ዛሬም መሠረት ነው ፣ ነገ የሚያርፍበት ፣
የትናንት መሠረት አይፈርስም በጸጸት ፣
ለነገውስ ምኞት ዛሬን ማን ነጥሎት ?
የዛሬው ውሳኔ ሚዛን ነው ለነገው ፣
ዛሬ ያልከበደ ነገ መቅለሉ ነው ።
ዛሬ እንደሠፈሩት ቢተርፍም ፣ ቢጎድልም ፣
ነገ ይሰፈራል ታሪክ ፍርዱ አይቀርም ።
ትናንትና ነገ የተያያዙበት ፣
ዛሬ ነው ስንሰለት ውሳኔ ያለበት ።
ከባዱ ውሳኔ ትልቅ ኃላፊነት ፣
የነገው ቅርጽ - መልክ የሚታነጽበት ።
ትናንት ነገ ፣ ዛሬ የሚለዩ አይደሉም ፣
ድርና ማግ ናቸው ፣ የታሪክ ራስ ጥምጥም ።
ነገ ዛሬ ሲሆን ዛሬም ትናንትና ፣
የዛሬ ቁራኛ ግልጽ ድንቁርና !

ገጽ ሰባት ላይ ይቀጥላል

— ተጠየቅ መስከረም ፣ — (*)

ተጠየቅ መስከረም ፣
ዛሬስ ዋዛ የለም !
አንተን ለመቀበል እንቁጣጣሽ እያልን ፣
ከርስ እንሞላለን ፣ እንሳከራለን ፣ እንጨፍራለን ።
አልገባኝም እኔን አንተ መወደድህ ፣
ስትገባ ስትወጣ ድግስ መቀበልህ ፣
ዶሮው ፣ በጉ ፣ ሰንጋው ይታረድልሃል ፣
ርጥብ ቁጠማና ደም መውደድህ ታውቆአል ።
እንስማው ተናገር ፣
የያዝከውን ነገር ።
ስጦታህ ምንድን ነው ? ለኛ ያመጣኸው ?
ክፈተው ማኅንህን ፣ እስቲ እንመልከተው ።
ለምለሙን ሣር እንደሁ ይጋጡት ከብቶቹ ፣
ለኛ ምን ይዘሃል ? ለኛ ለሰዎቹ ?
ሞት ሊጠፉ ነው ወይ ባዲስ ፍልስፍና ?
መድኃኒት አመጣህ ? ለሕመም ? ድህነት ? ለኛ ድንቁርና ?
ተጠየቅ መስከረም ፣ ያመት መጀመሪያ ፣
መነሻ ፣ መድረሻ ፡- የሰው ልጅ፡- የታሪክ መቁጠሪያ ።
ተጠየቅ መስከረም ማን አዲስ ይለብሳል ? ቡቱቶውን ጥሎ
ፎቅ ቤት ማን ይሠራል ? ጎጆውን አቃጥሎ ።
ተጠየቅ መስከረም ፣ - ያለፈው መስከረምን ምታሪክ ነገረህ ?
ምን ሰማሁ ፣ ምን አየሁ ፣ ምን ተሰማኝ አለህ ?

መዝገቡ ምን ይላል ? አንብበው ፤ እንስማው ፤
የቱ ያመዝናል ? ሥራ ነው ? ምኞት ነው ?
መስከረም ተጠየቅ !
ተናገር ! አትሳቅ !
ትተራው ተሙዋጦ በዳ ለታሰረው ፤
ለዚያ ለገበሬ ሳያርፍ ለሚሠራው ፤
ሚስቱና ልጆቹ እየተላቀሱ ለሚፈጽም ተግባር ፤
በጦር ግንባር ላለው ለዚያ ለወታደር ፤
ካልጋ ተቆራኝቶ ታሞ ለሚያጥረው ፤
ወይ አይሞት ፤ ወይ አይድን ስቃይ ለታደለው ፤
ለወላድዋ ድሀ ባልዋ ለሞተባት ፤
የልጆችዋ ረሀብ ሰቀቀን የበላት ፡
ምን ይዘህ መጥተሃል ?
ተናገር ፤ እስቲ በል !
በፍርሃት ፤ በስጋት ፤ ስቃይ ለሚበሉት ፣
ፍትሕ ይዘህ መጣህ ወይ ? ሕግና እኩልነት ?
ሰላም አመጣህ ወይ ? ነፃነትና ሀብት ?
ሰውን ልታድስ ነው ? ወይስ ልታሻግት ?
የዘንድሮው እከሊል ትጋት ነው ስንፍና ?
ችግር ደባል ነው ወይ ዘንድሮም እንዳምና ?
ተናገር ! ላዳምጥህ !
ትዝብት አይሰለችህ !
ለኔ ያመጣኸው በሳቅህ ገብቶኛል ፤
እንዲት ጥያቄ ናት ፦ ምን ሠራህ የምትል ።
ይጭንቅህ ! ይጥበብህ ! ግራ ይግባህ አንተም !
አንተም አልነገርከኝ ፤ - እኔም አልነግርህም ።

ይሙት በቃ ብሎ ታሪክ ፍርዱ አይቆምም ፤
የተቀበረውን ፤ ሬሣም አይምርም ።
ታሪክ ትዝብት ነው ፤ ፍሬው እንዲፋፋ ፤
እረም እንክርዳዱን መርጦ የሚያጠፋ ፤
ታሪክ ትምህርት ነው ፤ የጸጸት አለንጋ
ትውልድን ለእድገት ገፍቶ የሚያስጠጋ ፤
ታሪክ ፍርድ ቤት ነው ፤ የሕሊና ችሎት ፤
ሕያው ከሙት ጋራ የሚሙዋገትበት ፤
ታሪክ ማዕበል ነው ፤ የሚኾጎደጉድ ጎርፍ ፤
ሊታገድ አይችልም ገፍትሮ ነው የሚያልፍ !
ይሄዳል ፤ ይሮጣል ፤ ኃይል እየጨመረ ፤
ይንዳል ፤ ይክባል ፤ እያነጣጠረ ።
ጎረምሳና አሮጌው ዋና ልዩነቱ ፤
አሮጌው ትናንትን የሙጥኝ ማለቱ !
ዛሬ ለዛሬ ሲል ጎረምሳው ማርጀቱ !
አንድነቱ ደግሞ ነገ መረሳቱ !
ቂልነት ነው ፤ ትዕቢት ?
ወይስ ደደብነት ?
ነገ የሚፈርሰው ዛሬ እሚካበበት ?
የማታ ማታ ታሪክ ይረታ ፤
እንዴታ !
እንዴታ !

የሰው አውሬ ፣

ምን አለብኝ ብሎ ፣ ማን አለብኝ ብሎ

የማይቆጠብ ሰው ፣

ራሱን አታሎ ፣ ሰውንም አታሎ

የውሸት የከበረው ፣

የነፍሱን ኡኡታ የኅሊናውን ድምፅ አፍኖ ሸንግሎ

እንቅልፍ የሚወስደው ፣

ዓይንና ጆሮውን ከአእምሮው ገንጥሎ

ቅሬታ እማይገባው ፣

ሌሎች ሲበሳጩ ፣ ሌሎች ሲሸበሩ ፣ ብዙ ነገር ኀድሎ

ሞልቶለት ደስ ያለው ፣

ከዙሪያው መበስበስ ከዙሪያው መሻገት እሱ ተገንጥሎ

የማይቆረቁረው ፣

የሰው አውሬ እሱ ነው ።

የቁልቁለቱ ኃይል

አንዱ ነገር ካንዱ እየተጋመደ ፣

እየተዛመደ ፣

እየተዋለደ ፣

በመቆየት ብቻ ቀኑ እየረፈደ ፣

አዲስ አዲስ ነገር እየተለመደ ፣

ልኂይ እየበረደ ፣

ጭምቱ እያበደ ፣

ቁም ነገሩ ቀርቶ እየተቀለደ ፣

በቁልቁለት ጉዞ ሁሉም ተጣመደ ።

ተያይዞ ነጐደ ፣

እየተካከደ ።

ዳገት ላይ ሰው ጠፋ ፣ አቀበት ከበደ ፣

ሁሉም በሽርተቴ ቁልቁለት ወረደ።

ሰው ተዋረደ ፣

ገንዘብ ተወደደ ፣

በምኑቱ ፣ በፍቅሩ ፣ በክብሩ ነገደ ፣

በቁልቁለቱ ኃይል እየተገደደ ።

—ሰው አልተፈጠረም—

እንዳይጥ በጉድጓድ በጨለማ እንዲኖር ፤
ሳይሞት ፤ ሳይገነዝ በቁሙ እንዲቀበር ፤
በፍርሃት ፤ በጭንቀት ፤ በሥጋት ለመኖር ፤
ሰው አልተፈጠረም ፤ ክርስቶስ ይመስክር!
መቃብር አይሞቅም ፤ ኑሮም ሊሆን አይችል ፤
ሥጋውስ ይፈርሳል ፤ ምስጥ ይመገበዋል ፤
ነፍስንና አእምሮን በመቃብር ማኖል ፤
ውርደት ነው ፤ ቅሌት ነው ፤ መጨረሻው ወንጀል!
ባራት እግሩ እንዲሄድ ፤ አፈሩን እንዲግጥ ፤
እያነፈነፈ እንደውሻ እንዲሮጥ ፤
ሰውነቱን ፤ ክብሩን በሆዱ እንዲለውጥ ፤
ሰው አልተፈጠረም ፤ እንዲኖር በቅልውጥ!
በተወለደበት በአደገበት «ዕድል»
እጆቹን አጣምሮ ሥቃይ እንዲቀበል ፤
ከጥሬ ሳይወጣ እንዲሞት በቅማል ፤
ሰው አልተፈጠረም ፤ ለዚህ «ዕድል» በደል!
ከሥጋ እሚወለድ ተባይ ለመመገብ ፤
አንጀቱ ደርቆበት ፤ እሱ ራሱ ሳይጠግብ ፤
እውቀት እያነሰው ፤ አንጎሉ እንዲደድብ ፤
ሰው አልተፈጠረም እንደዚህ ላለው ግብ!
ቀና ብሎ እያየ ቀና ብሎ እንዲሄድ ፤
በአእምሮ ፤ በመንፈስ እንዲያድግ ፤ እንዲራመድ ፤
እየተሻሻለ ትውልድ ከትውልድ ፤
እንዲገሠግሥ ነው ሳይቆም ሳይታገድ!
የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነፍስና አእምሮው ፤
በሥላሴ አርአያ ሆኖ የተሠራው ፤
ከመልአክ በላይ ነው ሰውስ በተፈጥሮው ፤
መንፈሱን አርክሶ ክብሩን ካልገፈፈው!

—የወፍጮ እንጉርጉሮ—

ወይ ዕድል ! ወይ ዕድል ! ወይ ዕድል!
ምን ሳረግ አገኘኝ? ወይ በደል! ወይ በደል!
እሜቴና ጌቶች
ይሆኑ ወይ ሰዎች!
ወይ ዕድል! ወይ በደል!
እኔም ከነሱ ጋር
ከሰው ነው እምቆጠር!
ወይ ዕይል! ወይ በደል!
ተቃቅፈው ተኝተው ፤
ብልኮ ደራርበው ፤
ወይ ዕድል! ወይ በደል!
ተኝተው ሲያኮርፉ ፤
በፍቅር ሲላፉ!
ወይ ዕድል! ወይ በደል!
እኔ እዚህ እፈጫለሁ ፤
በምብርክ እድራለሁ!
ወይ ዕድል! ወይ በደል!

ስፈጪው በንባዬ ፣ ሳቦካው በንባዬ ፣ ስጋግር በንባዬ ፣
ያምግቸው ይሆን ወይ ? አወይ አበሳዬ !

ወይ ዕድል! ወይ በደል!

እንባዬና ላቤ ይወርዳል ባንድነት ፣
የተኙት ሊበሉ የኔ እንደዚህ መልፋት !

ወይ ዕድል! ወይ በደል!

የታባክ አንተ ሆድ ! አፈር ብላ ሆዴ!
ላንተ ስል ተጠቃሁ! ወላለቀ ክንዴ!

ወይ ዕድል! ወይ በደል!
አይ ዕድል! አይ እግዜር!

የኔን አጥንት ፍቀህ ሌላውን ማወፈር !

ወይ ዕድል! ወይ ዕድል! ወይ ዕድል!
ምን ሳረግ አገኘኝ? ወይ በደል! ወይ በደል !

ማኅበር

ሰማይ ፣ መሬት ፣ ጥንቸል ገቡና ማኅበር ፣
ሁሉም «ከፈልን » አሉ ከጥንቸልዋ በቀር ።
መሬት ፋታ አልሰጠም ፣ ከፉኛ አስጨነቃት ፣
መብል ፣ መጠጥ ቀርቶ መቆሚያም አሳጣት ።
መሬት በንዝንዝ አናውጠ ናላዋን ፣
ሙልጭ አርጎ ጠባት ላብዋን ፣ ወዝዋን ፣ ደምዋን ።
ሰማይ አልተገኘም ፣ ከፉኛ ራቀባት ፣
በእርግጫ መትታው በቅሎ ሳይቸግራት !
ከላይና ከታች እየተጣቀሱ ፣
የድሀዋን ጥንቸል እንባዋን ጨረሱ ።
ወዝዋን ፣ ላብዋን ፣ ደምዋን ፣ ሥጋዋንም መጥጠው
ማኅበሩ ጭራሽ ቅምም አላላቸው ።
ደመና አንዳንዴማ ሰማዩን ሲጋርድ ፣
አንበሳም አይችለው የመሬትን ሞገድ ።
ጥንቸልዋ ፍበዘች ፣ ደቀቀች በድካም ፣
የመሬት ጥልዋ እንጂ ፍቅርዋስ አልተገኘም ።

«መሬት እንባ ጠጣ ፤ ሰማይም ላቤን ፤
ሥጋዬም ይጨመቅ ፤ ተውት አጥንቴን ።
እኔን ከበላችሁ የማኅበሩን አባል ፤
ምን ማኅበር ሆነ ለናንተም ያስፈራል !
ማኅበሩ እንዲጸና ፤ እንድንተማመን ፤
«የኔ» የምለው ስጡኝ ፤ ጠጡ እንባ ላቤን ፤ »
እያለች ብትማጥን ደካማዋ ጥንቸል ፤
ከንቱ ጩኸት ሆነ ፤- «ስምዓነ ዳኀን ! ስምዓነ ቤል !
ዳኛ ከየት ይገኝ ለጥንቸልዋ ምሬት ?
በመሬት ተቀምጦ ማን ይፍረድ በመሬት ?
ስትሮጥ ጥንቸልዋ ትልቅ ባሕር አገኘች ፤
ዘልላ ገባችበት ፤ - «የሙጥኝ ! » እያለች ።
ከት እያለ ስቆ አፍኖ ቀበራት ፤
ሰማይና መሬት አደረጓት ራት ።
ሰማይና መሬት እንዴት ጥንቸል በልተው ፤
መቼም አይጠቅማቸው ፤ ከደላን ብለው ነው ።
ግን ካዘወተሩት እየጣፈጣቸው ፤
በግፍ ለሚያጉረው ይብላኝ ለሆዳቸው !

—ቻይ መሬት—

አልጋዬ ይሎሖሃል ፤ ስተኛበት ፤
ወንበሬም ይንጣጣል ፤ ስቀመጥበት ፤
ጫማዬ ያለቅሳል ፤ ስረግጥበት ፤
እኔን ፤ አልጋዬን ፤ ወንበሬን ፤ ጫማዬን የተሸከመች መሬት
ዝም ብላለች ፤ ድምፅም የላት ፤
በድንነት ይሆን ? ወይስ ትዕግሥት ?
ያም ሆነ ይህ ፤ መሬት ቻይ ነች ፤
በላይዋ ሲፋለሱ ፤ ሲላቀሱ ታያለች ፤
እያዘነች ፤ ሁሉንም እየታዘበች ፤
«ጎንበስ ብሎ ባየኝ ! » ትላለች ፤
ያማ የት ይቀራል !- ታውቃለች ፡-
እስቲተኙ ካልተቀመጡና ካልረገጡ አይመች !

የገበሬ እንጉርጉሮ

የሕግ ሚስቴ መሬት ፤
አልረባችኝም ፤ ምን ላርጋት ?
ውብ ፤ ደማም ፤ የማትጠገብ ፤
ሁሉንም የምታስገበግብ !
አጣላችኝ ከብዙ ሰው ፤
ያገኘት እንኳን ጥቂት ነው ።
በሕግማ የኔው ናት ፤
በጥሎሽ ያገባሁአት ።
የማያበሉ ፤ የማያጠጡ ፤
እየሰረቁ የሚያማግጡ ፤
አያል ሆኑ ፤ ምን ላርጋቸው ?
ቦዘኖች ሚስቴ ፤ በጃቸው ።
ደግነታቸውም አላማረኝ ፤
ክብሬን በጉቦ ገፈፉኝ !
ዘሩ የነሱ የማርሳት እኔ ፤
የሚስቴ ወዳጆች ጭካኔ !
ፍሬው ዘሩን ሲከተል ፤
ቀረሁ በልፋት ፤ - አለመታደል !
በሚስቴ ፍሬ የእንጀራ አባት ፤
የወላድ መካን ሆንኩባት ።
ሚስቴን ብፈታት ፤ መሬትን ፤
ለሁላችንም አይበጀን ።
የሚስቴ ወዳጆች ኃጢአታቸው ፤
ለጻድቃን ይተርፋል ፤ ሀይ ! በሉአቸው ።

እረ ስማ እግዚአብሔር !

እረ ስማ እግዚአብሔር !
ተቸገረ ፍጡር !
እስከመቼ ድረስ ዝም ብለህ ታያለህ ?
አይሰለችህም ወይ አቤት ! አቤት ! ሲሉህ ?
ችግርህ ይሆን ወይ ? ብልሃቱ ጠፍቶብህ ፤
ባንተው እጅ ሥራ በገዛ ትንፋሽህ ፤

አንተ እኛን ፈጠርከን ፤
እኛ ተንኮል ፈጠርን ፤
ተጎልተን ቀረን ፤

እንዲሁ ተፋጠን !
እረ ስማ እግዚአብሔር !
ተጨነቀ ፍጡር !

ትካዜ ፤ ድንጋጤ ፤ ጸጸት ገባህ እንዴ ?
አንተው በሠራኸው ባዋቂው ወንበዴ ?
ተናድደህ ይሆን ወይ ? በታመመው ዓለም ፤
ፍርድህን ወስነህ ልታጠፋው ፍጹም ?

ምነው እንዲህ ዝም አልክ ?
እሺ ነገን ተማርክ !
ርቀት ነው ንቀት ?
ጭካኔ ነው ፍርሃት ?
እረ ስማ እግዚአብሔር !
ተቸገረ ፍጡር !
ሥራ በዝቶብህ ነው ? ወይስ ረስተኸን ?
ቲያትር እያየህ ትስቅብን ይሆን ?
ጻድቃን ፤ መላእክቱ ምን ምክር ያቀርባሉ ?
እያማልዱም ወይ ስለት እየበሉ ?
ኃይለኞች ምን አሉህ ?
ሀብታሞች ምን ሰጡህ ?
እንደዚህ ጭጭ ያልከው !
ወይ እንኳ እማትለው ?
እረ ስማ እግዚአብሔር !
ተሸበረ ፍጡር !
በስምንተኛው ሺህ ቴክኒኩ ሲሻሻል ፤
ስልኩ ጸሎታችን እንዴት ይበላሻል ?
ለውጠህም እንደሁ የስልክህን ቁጥር ፤
ላክልን ልጅህን ፤ ደግሞ እስቲ ያስተምር ።
እኛኮ ተስፋ አለን ፤
ትሰማለህ ብለን ።
ኸረ ስማ እግዚአብሔር !
ተቸገረ ፍጡር !

እነዚያ ሦስት ወጣት

እነዚያ ሦስት ወጣት ፤
የሞቱት ለሰው መብት ፤
ያሜሪካ ጸጸት ፤
የሰው ልጆች ኩራት ፤ -
ፍቅር አቃጥሎአቸው የመብት ፤ የነፃነት ፤
ሲኦል ሚሲሲፒን ለማንጻት በመስዋዕት ፤
ሚሲሲፒ ገቡ ፤ - ገሃነመ እሳት ።
ፍርሃት ፤ ስጋት ፤ ዶሮ ማታ እያሉ ራስን ማታለል ፤
ሳያስሩአቸው ቀሩ ፤ መታደል ፤ ወይ አለመታደል !
ሰው ሁሉ ተኝቶ ፤ እናንተ ነቅታችሁ ፤
ሽማግሌዎቹን ፤ ሊቆቹን በልጣችሁ ፤
መሞትን መርጣችሁ ፤
ለታሪክ በቃችሁ ።
በስምንተኛው ሺህ በዚህ ክፉ ዘመን ፤
በምግባር ፤ በሕይወት መግለጽ ሃይማኖትን ፤
ማን አስተማራችሁ የሳት ራት መሆን ?

የጥቁር ደም አይደል ፣ የነጭ ደም አይደል ፣
የሰው ደም ፈሰሰ ፣ ፈሰሰ ለሰው ሲል ።
ምስጦች አትንኩአቸው ፣
ቆስሎአል አካላቸው ፣
ፈስሶ አልቆአል ደማቸው ፣
ሰማዕታት ናቸው ።
ምድረ ሚሲሲፒ ያሜሪካ ሐፍረት ፣
ደማቸው ያቃጥልሽ ! ይሁንሽ መድኀኒት ።
የግዜር ቃል ኪዳኑ የተሰጠው ለኖኅ ፣
«ኢያማስና ለምድር ዳግመ በማየ አይኅ ፣ »
ሚሲሲፒን በጃት ፣ ወፈረች በመስዋዕት ።
ጦር ይቀርቀርበት በኀሊናሽ እምብርት !
እንቅልፍ አይውሰድሽ !
እንቅልፍም ቢይዝሽ ፣
ቅዠት ይቀስቅስሽ !
ታላቅዋ አሜሪካ የዴሞክራሲ ቁስ ፣
እንባሽ ለማን ይፍሰስ ?
«የገደለው ባልሽ ፣
የሞተው ወንድምሽ !»
ቅጥ አጣ ሐዘንሽ ።
እንዴት ብዬ ልጥላሽ ?
እንዴትስ ልውደድሽ ?
ጽድቅና ኩነኔ መንታ ልጆች ወልደሽ ፣
ለጉድ የኀለተሽ !
ለወጉ እግዜር ያጥናሽ !

እንዲያው ዝም !

ክረምት ነበረ ፣ ሐምሌ ነበር ወሩ ፣
ሰማዩ ተቀዶ በሰብሶአል አገሩ ፣
ይወርዳል መዓቱ !
ጨቅይቷል መሬቱ ።
ሰው ይሯሯጣል ፣
መጠለያ ጠፍቷል ።
አንዳንዱም ፡- ዝናቡ እያጠበው ልብሱን ሁሉ ዘልቆ ፣
ጨርቅና አከላቱን አንድ ላይ አጣብቆ ፣
ዝም ብሎ ይሄዳል ፣
ዝናቡን ንቆታል ።
ከመዓቱ ዝናብ እንዲያ ከሚወርደው ፣
የበለጠ ችግር እሆዱ ውስጥ አለው ።
በየሰው ፊት ላይ አሳሩ ይታያል ፣
ደስታን ኀርፍ ይዞት የሄደ ይመስላል ።
ታዲያ ፡- በመኪና ሆነን ከልጆቼ ጋራ
እየተንፈላሰስን ስንስቅ ስናወራ ።
የኛንም ደስታ ኀርፎ እንዳይወስድብን ፣ በመኪና ይዞን !
የዙሪያችን አሳር የማይነካን መስሎን !
መስሎን ! መስሎን ለኛ ብቻ የቀረ ደስታ !
ማስተዋል ሲመጣ በደስታ ፋንታ ተተካ ዝምታ ።
የሦስት ዓመት ልጄ ድንገት ኩስትር አለች ፣
ዙሪያዋን ልብ አርጋ ጥያቄ ጠየቀች ፡-
«እነዚህ ሰዎች ለምንድን ነው ፣
እንደኛ መኪና የሌላቸው ? »

ጥያቄው ቀላል መስሎኝ ፤
«ገንዘብ የላቸውማ !» አልኩኝ ።
«ገንዘብ የሚገኘው ሲሠሩ አይደለም ?
እነሱ ታዲያ ለምን አይሠሩም ?»
ስትለኝ ጊዜ ተገነዘብሁት ፤
ከባዱን ነገር እንዳቀለልሁት ።
«ከመሥራትማ መች ያርፋሉ ፤
ሌት ተቀን እኮ ይለፋሉ ። »
ብዬ ሳስረዳ ፤ «ታዲያ ገንዘቡስ ?»
ስትለኝ ጊዜ ምን ልመልስ ?
«የነሱ ድካም ፤ የነሱ ልፋት ፤
ሥራ አይደለም »ልበላት ?
«ልፋቱን ትተው ሥራ አይሠሩም ?»
ያለች እንደሁ መልስ የለኝም ።
እንዲያው ዝም !
ጥያቄውን ከነመልሱ ድርግም !
እንዲት ጥያቄ በመኪናችን ውስጥ ገብታ ፤
የደስታችንን ሙቀትና ድምቀት አስወጥታ ፤
ብርዱ ተሰማን ፤ ገባን ትካዜና ሐዘን ፤
የሐምሌን ጭጋግ አላመለጥነውም ፤ ያዘን ፤
አሳሩ እንደተጋባብን ታውቆናል ፤
እንዲያው ዝም ብለናል ።

---ወይ እንገላገል !

እንደሚነድ ፍልጥ እንደሚንቀለቀል ፤

በሳት ተያይዞ ፤ እሳት የሚመስል ፤

ልቤ ሲንቦገቦግ ሲሰማኝ ሲከስል ፤

አከላቱ ሲግል

ነፍሴ ልውጣ ! ልውጣ !- እያለች ስትዝል ፤

ሕይወት ከሞት ጋራ ሲመናጨቅ በጥል ፤

ጥላቻና ፍቅር መንፈስ ሲገነጥል ፤

ዓየሩ ጭስ ሲሆን እፍኖ የሚገል ፤

እኔ ልቤ ቆስሎ ስሆን የሰው ቁስል ፤

የተበደለው ሰው ተስማምቶ ከበደል ፤

ለበደል አድልቶ ከኔ ጋር ሲታገል ፤

ወይ አይገላግሉን ! ወይ እንገላገል !

—ብቸኛነት—•—

ቀኑ ተሰናብቶአል ፤

ጨለማው በርትቶአል ፤

ጨረቃ የት ጠፋች?

ምን ሆኑ ኮከቦች?

ጅቦቹ አይፈነጩ!

ውሾቹ አይንጫጩ!

ጨለማው ፍጹም ነው ፤ ነፋስ ጭራሽ አይነፍስ !

ዛፉ አይወዛወዝ ፤ አንድ ወፍ አይላወስ!፡

ሁሉም ጸጥ!

በያለበት ለጥ!

ሰው ሁሉ ምን ነካው?

ድምጹ እንዲህ የጠፋው ?

እኔንስ ምን ነካኝ?

እንቅልፍ የማይወስደኝ ?

እኔ ብቻዬን ነኝ በዚህ ደረቅ ውድቅት ፤

ልቤ እያቃተተ ጠልቶ ብቸኛነት ።

ሰው አለ ወይ ባገር?

ማረፊያ ለፍቅር?

ፈላጊና - ተፈላጊ ሁሉ ፤

ቀናው ወይ በሙሉ?

የቀረ የለም ወይ ባገሩ እለኔ?

በምኞት ኩነኔ!

እኔ እንደዚህ ስዋኝ ባሳብ በትካዜ ፤

የት ይሆን ያለሽው አንቺ ይህን ጊዜ?

ምን ታደርጊ ይሆን?

እንገናኝ ይሆን?

መች ይሆን ዕለቱ?

ምን ይሆን ሰዓቱ?

የትስ ይሆን ቦታው?

እንዴት ይሆን እውቂያው?

እጠብቅሻለሁ ልቤን እያታዘዝሁ ፤

አትቅሪ! ፈልጊኝ! እፈልግሻለሁ !

መሰላል መውጣት

መሰላል ለመውጣት ፤
አለው ትልቅ ብልሃት ።

የላዩን ጨብጦ ፤
የታቹን ረግጦ ፤
ወደላይ መመልከት ፤
እጆቹን ዘርግቶ በኃይል መንጠራራት ፤
ጨብጦ መንተት የላዩን !
ላዩ ታች እንዲሆን !
አንድ በአንድ እየረገጡ ፤
መሰላል የወጡ ።

ብልሆች የማይጣደፉ ፤
ሞልተዋል በያሉ !
ዘርግተው የጨበጡትን መርገጥ ፤
የመውጣት ሕግ ነው የማይለወጥ !
ሲወርዱ ግን ያስፈራል ፤
የረገጡትን ያስጨብጣል !

ቆሜ እየዋለሁ !

ስንዝ በጎዳና ፤
አገኘሁ መንገደኛ ፤
ዕድሜው ከናሳሩ ፤
የሚታይ በግንባሩ ።
«እንዴት ነው ? » አልሁት « መንገዱ
የመውጣት ፤ የመውረዱ ፤ »
«ለኔ ፤ ከንግዴህ ወዲያ ቁልቁለት ነው ፤
መውረድ ብቻ ነው የቀረው ።

አንተ አፋፉን ካለፍከው ፤
አያደክምህም ሴላው ። »
ብሎ መለሰልኝና ፤
ሊሄድ ሲል እንደገና ፤
ጠየቅሁት ፤ «ስንት አፋፍ አለ ?»
«እንደመንገድህ ነው ፤ » አለ ፤
«እንደፍላጎትህ ፤
ማንም አይከለክልህ ፤

ታች ታቹን ከሄድህ አፋፍ አትወጣም ፤

አፋፍ ከወጣህ መውረድ አይቀርም ።

ሜዳ ሜዳውን ሰላም ነው ፤

አፋፉ ላይ ነው ጭንቀት ያለው ። »

«እባክህ ምከረኝ !

የትኛው መንገድ ነው የሚሻለኝ ?»

ብዬ ብጠይቀው ፤

ጭንቀቱ ፊቱን ሞላው ።

«መንገዳችን ለየቅል ፤

አንተ ዳገቱን እኔ ቁልቁል ፤

የኔ ላንተ አይሆንም ፤

የሚሻልህን አላውቅም ። »

አለኝና ቀጠለ ፡- ቁልቁለቱን ፤

እኔም ቆሜ እየዋለሁ ፡- አቀበቱን !

የት አለ ወንዱ ልጅ ? *

የት አለ ወንዱ ልጅ ኮስታራው ፤ ኮፍናናው ?
ልጂቱ ልጅ ትሁን አለዚያ እምቢ እሚለው !
የት አለ ወንዱ ልጅ እውነት ክብሩን ለብሶ ልቡን የሚነፋው!
ግርማና ሞገሱ ግምባሩ ላይ ያለው !
የት አለ ወንዱ ልጅ ችግር የሚደፍረው ?
ክብሩን ለምቾት ሲል በማንቲም ያልሸጠው !
የት አለ ወንዱ ልጅ ማተቡን ያሰረው ፤ ግትሩ ፤ ነፍስ ያለው
ሞት አይቀርም ብሎ በቁም ነገር ሁሉ የማይወላውለው ፤
የት አለ ወንዱ ልጅ ጥቃት የማይወደው ?
እምቢኝ ! አሻፈረኝ ! አትንኩኝ ! የሚለው ፤
የት አለ ወንዱ ልጅ ሽለላ ፤ ፉከራ ደሙን የሚያፈላው ?
የሥልጣኔ ትል ወኔውን ያልበላው !
የት አለ ወንዱ ልጅ ሱሪ የታጠቀው ?
እጁን ሳይሰነዝር ባይኑ የሚማታው !
የት አለ ወንዱ ልጅ እንዳባቱ ያለው ?
ሐሞትና ልቡን ለሆዱ ያልሠዋው !
የት አለ ወንዱ ልጅ ሴትነት ታቦቱ ፤ መስጊዱ ያልሆነው ?
ዳሌ ባየ ቁጥር ብርክርክ ፤ ዝልፍልፍ ፤ ስብርብር እማይለው
የት አለ ወንዱ ልጅ ?
ለገበያ እማይበጅ !
ታዝሎ ያላዘለ !
ወንዱ ልጅ የት አለ !
ወንዱም የሚሸጥ ነው ፤ ሴቱም የሚሸጥ ነው ፤
ገንዘብ ያለው ይግዛ ፤ ይገዛ የሌለው !

ግራ ገባኝ

እንበሳውን ልሁን ፤ ጡንቻዬን ላፈርጥም ፤
እንዳደቅቀው በክርን ይህንም ፤ ያንንም ።
እባቡን ልሁነው ፤ ልቤን እግር ላርገው ፤
ሰርስሬ ፤ መርዤ ፤ ደሙን እንድጠጣው ።
ምስጥ ልሁንና ሬሣውን ልብላ ፤
የሞተው ሞልቶልኝ ከአለው አልጣላ ።
እስስቲቱን ልሁን ከሁሉም ልዳራ ፤
መስሎ መብላት ሳለ ጠላት ለምን ላፍራ !
ጥንቸልዋን ልሁነው ፤ በፍርሃት ልሽቆጥቆጥ ፤
ሳገኝ እየበላሁ ሲመጡብኝ ልሩጥ ።
ውሻ ልሁንና ይቁላላ ጅራቴ ፤
ግብዙን ላስደስት ፤ ይጫወት በእምነቴ ።
አህያውን ልሁን ፤ ልደድብ በትዕግሥት ፤
ይነርቱኝ ይዘው ፤ ይጫኑብኝ ኩበት ።
እውቀት ፤ እውነት ፤ እምነት ፤ ቅንነት ፤ ግልጽነት ፤
ዋጋቸው ምን ይሆን?— የሰውነቴ ሀብት ።
እውነተኛ ልሁን ? ወይስ ልሁን ታማኝ ?
የቱ ያኮራኛል ? የቱ ነው እሚያበላኝ ?
ለምን ላስብ ቀድሞ ? ምንስ ያሰጋኛል ?
ለሆዴ እንደሆነ — ሕሊናና አእምሮን መሸጥ ይበቃኛል ።
ልብላ ? ልበስብስ በቁሜ ? ክብሬ ልከበር ?
ወይስ ልሙትና ኮርቼ ልቀበር ?
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ መሆኑን አውቃለሁ ፤
አልቀበር እንጂ እኔኮ ሞቼአለሁ !
ዓላማው ጠፋብኝ ፤ ፍጹም ግራ ገባኝ ፤
መልአክነት ስመኝ ፤ ሰው መሆን ከበደብኝ !

ሞት ማለት፡-

ተንጋሎ መተኛት ፤ አለመንቀሳቀስ ፤
ፍጹም የእንቅልፍ ዓለም ፍጹም የሕይወት ቀውስ ፤
አለመደሰት ነው ፤ ተከፍቶ አለማልቀስ ፤
የሬሣ እኩልነት ፤ ርኩስ የለ ቅዱስ ፤
በኅብረት መበስበስ ፤ በየቀኑ መፍረስ ፤
ሞት አለመስማት ነው ጆሮ ዳባ ልበስ ፤
ክርስቶስ ሲሰቀል ፤ ሲፈታ በርናባስ ።

ሞት ማለት ፡-

አለመናገር ነው ጭው ያለ ዝምታ ፤
የመቃብር ሰላም የሬሣ ጸጥታ ፤
ደሀ በሰሌኑ ማጥን ገብቶ ጌታ ፤
የውሸት ልዩነት ተጋድሞ በተርታ ፤
አይመሽ ወይ አይነጋ ፤ ጠዋት የለ ማታ ።
ሐዘን የለ ለቅሶ ፤ ደስታ ፤ ፈገግታ ፤
ዘፈኑና ለቅሶው የምስጥ ሹክሹክታ ።

ሞት ማለት ፡-

አይረገዝበት ፤ አይወለድበት ፤
የመቃብር ዓለም ፤ ጭንጋፍ ፤ የጭንጋፍ ቤት
የሰው ልጅ አንደበት ትል የሚሆንበት ፤
ክርክር የለበት ፤ ውድድር የለበት ፤
ውሸትና እውነት በማይበርድ ፍትወት የተሳሰሩበት
የድብቅብቅ ዓለም ምሥጢር የበዛበት ፤
ሁሉም በየጉድጓድ የተሸሸገበት ።

ሞት ማለት ፦
አለመንቃንት ፣ አለማንቃንት ፣
እንደድንጋይ መድረቅ ፣ ደርቆ መወላለቅ ፣
ክብርና ውርደትን ለይቶ አለማወቅ ፣
አዘቅት ውስጥ ተኝቶ በክፋት መጥለቅለቅ ፣
በተዋኅዶ መልክ ጠላትና ወዳጅ አብሮ ሲደባለቅ
ድፍርሱ ከጠራው ባሕርዩ ሲደበቅ
የሩቁ ሲጠጋ የቅርቡ ሲራራቅ ፣
ሞት አምሮት ሲጠፋ በልጦ ለመመረቅ ።

ሞት ማለት ፦
ሞት አለመስጋት ነው የማይለሽ ዓለም ፣
ድንጋይ ተሸክሞ በውሀ ላይ መቆም ፣
ጤንነት የለበት ፣ አያጠቃው ሕመም ፣
ትዝታ የለበት ፣ አይታይበት ሕልም ፣
ቡቃያው አያሽት ፣ ፍሬው አይለመልም ።
ዝናብ አይዘንብበት ድርቀት ነው ዘላለም ።
ማንም አይጎዳ ማንም አይጠቀም ።

ሞት ማለት ፣ የሞት ሞት ፦
አእምሮ ፈራርሶ
ኀሊና በስብሶ ፣
ሰውነት ረክሶ ፣
እንደግም ፣ እንደጥንብ ፣
የጭልፊቶች ምግብ ፣
የሞት ሞት ይኸ ነው ፣
ትንሣኤ የሌለው ።

እምላክስ በኔ ላይ የግፍ ግፍ ሠራብኝ በጣም ጨከነብኝ ፣
የንባ ጉድጓድ ብቻ ዓይኖች ፈጠረልኝ ፣ ጨለማ አለበሰኝ
እንዳላማው ብሎ እንዳላታክተው ፣ በፍርሃት ቃል ነሣኝ ፣
ዕውር ዲዳ አረገኝ ፣ ከውስጥም ፣ ከውጭም ክፍኛ መረገኝ ።
ጨለማ ብርሃንን አፍኖ ካሰረው እንደበት ሀሳብን ሰንጎ ካገደው
መኖር አይባልም ፣ የሚል ሰው አይጠፋም ፣ እኔም አልጣላው ፣
ፍርዱን ያጎደለው የብርሃን አምላክ ነው ፣
ዕውር ዲዳ ፣ አድርጎ እኔን የፈጠረው ።
የደላቸው ሰዎች ጊዜውን ሲለዩት በቀንና ሌሊት ፣
ትናንት ፣ ዛሬ ነገ ፣ እያሉ ከፍለውት ፣
ሁሉም ያው ነው ለኔ የለውም ልዩነት ፣
ዕውር ፣ ዲዳ ሆኜ ጊዜ እማያልቅበት ፣ ጊዜ እማያልፍበት ።
የደላቸው ሰዎች በቋንቋ በቃላት ከፍለው ድምፁን ሁሉ
ያሰቡትንና የተሰማቸውን አብረው ያወራሉ ፣ ወይ ይጻጻፉሉ ፣
ለኔ ሁሉም ያው ነው ፣ ጩኸት ነው በሙሉ ፣
ዕውር ፣ ዲዳ ሆኜ የማይለይልኝ ሚዳና ገደሉ ።
ኅሊናዩ በርቶ ዓይኔ ጨልሞብኝ ፣
ባሳብ ተጥለቅልቄ አፌ ተመርጎብኝ ፣
ስጨነቅ ፣ ስጠበብ ፣ ከጨለማ በቀር ጓደኛ ጠፍቶብኝ ፣
ዕውር ፣ ዲዳ ሆኜ ምን እንድነግራቸው ? ምንስ እንዲነግሩኝ

—የሞተ ኅሊና—

የማይጣላ ኅሊና ያለው ፣
እንዴት የታደለ ነው !
እግዜር ብቻ ነው ኅሊና የሌለው
የማይሳሳት የማይቆጨው ።
ሰው ፣ ሰውነቱ ፣ ጭንቀቱና ልፋቱ ፣
ኅሊናው ከስሜቱና ከፍላጎቱ መጣላቱ ፣
የሚረሳ ፣ የሚሳሳት ፣ የማይታየው የፊቱ ፣
የሚወድ ፣ የሚጠላ ፣ የሚፈራ ፣ ኧረ ስንቱ!
ከሳሽ ተከሳሽ ዳኛ መሆን
እንዴት ይችላል መበየን?
ሲያፍነው ማን ኅሊናውን
አይለይም ጨለማውን ከብርሃን !
ኅሊናውን የገደለ ሰው
ማን ሊቀረው? ምን ሊያቅተው?
የጉልበቱ መሣሪያ ነው ፣
ጊዜ ጉልበቱን እስቲሰብረው!
ራስ ካልከሰሰና ካልተከሰሰ በእውነት
ምን ያደርጋል ዳኛ ቢኀለት?
ሙግትስ በሌለበት
ማን ያውቃል «ፍርድ »ማለት!
ኅሊና ሲበሰብስ ታፍኖ ቢቀበር
ምን እንዳይቀር !
የሞተ ፣ ሬሣ ይዞ መኖር
ያስከፋል ፣ ወይ ችግር!
ሰው መች ይቸግረዋል ብልሃት?
ትልቁ መድኃኒት ፣ መርሳት!
መርሳት ! እያዩ አለማየት!
መርሳት ! አለመስማት !

—ምጽዓት—

ባሳብ ባሕር ዘፍቆ የሰው ልጅ ሲጨነቅ ፣
ሃይማኖት ሲራብ ፍልስፍና ሲረት ፣
ነፍስ እምነትን አጥታ ፣ መንምና በችጋር ፣
እውነቱ ሲያሳፍር ሲያስጠላ ፣ ሲያስመርር
ኃይል ክፋት ሲሆን የደካሞች ጭነት ፣
ፍቅር ጥምቡን ጥሎ ሲገዛ እንደኩበት
ፍርሃት ትዕግሥት ሆኖ ድንቁርና ኩራት
ውርደትም ትሕትና ጮሌነትም እውቀት
ትምህርትም ጌጥ ሆነ ያውም የተውሶ
ስንፍናም ጨዋነት ሰውነት ረክሶ ፣
ማተብ ክርስትና ነጭ ጥምጥም ክህነት ፣
ሀብት ብልጽግና ምቾት ትልቅነት ፣
ምኞት ተስፋ ሆኖ መቃብርም ኑሮ ፣
እንጉርጉሮው ዘፈን ዘፈኑ እንጉርጉሮ ፣
ባዳ ሆነ ዘመድ ባለቤቱ እንግዳ
ሆድም አምላክ ሆነ አውሬውም ለማዳ ፣
ገንዘብ ዳኛ ሲሆን ወንጀል ከሳሽ ሆኖ ፣
ግብዝነት ደላው ጽድቅ ተኩንኖ ፣

ወጣትነት ጫጩ እርጅና እየለማ ፤
የኋሊት መገሥገሥ የጊዜው ዓላማ ፤
ከራስ በላይ ነፋስ ትልቁ ሃይማኖት ፤
ዘረፋን ሲያውጀው ቂም ሲያስረግዝ ጥቃት ፤
ዓይን አያይም አሉ ጆሮም አያዳምጥ ፤
ተለጉሞ እንደበት ሁሉም ይዘታል ምጥ!
በቁንጣን በስካር ጥቂቶች ሲንሩ
ብዙዎቹ ደግሞ በረሃብ መንምነው በቁንጫ ሲያርሩ
የደሀ እንባ ሲጎርፍ መሬቱ ሲሸበር
ፍትሕ በሌለው ፍርድ ሚዛኑ ሲሰበር ፤
ዝብርቅርቁ ወጣ!
ሕይወት ትርጉም አጣ!
እረ የት ነው ጉዞው? ዓላማው ምንድን ነው?
ቀድመው የሄዱትን ምነው አናያቸው!
የት ገቡ? የት ጠፉ? ፋና እንኳን አይታይ ፤
ብልጭ የሚል የለ ከመሬት ከሰማይ!
መንገዱ ጠበበ ትርምስምሱ በዛ ፤
እረታው ኡኡታው ቀለጠ እንደዋዛ ፤
መሬቱም ዓየሩም በክፋት ጠነዛ ፤
ጥላቻና ቂሙ በሰፊው ተነዛ ።
እምቢልታው ሲጣራ ነጋሪት ሲያገሳ ፤
የአለው ሁሉ ሞቶ የሞተው ሲነሣ ፤
ምጽዓት መድረሱ ነው ፤ ሊስተካከል ነው ፍርድ፤
በግና ፍየሉ ሊለዩ በገሃድ!

ስብሐት ለጨለማ (*)

ስብሐት ለጨለማ ፤ ለብርሃን ዋዜማ !
ጨለማ ! የስርቆሽ ውድማ ! የግብዝ ከተማ !
ጨለማ ! የክፋት ፤ የተንኮል ፤ የጭካኔ አለኝታ !
የወንጀል ነፃነት ! የኃጢአት ደስታ !
ይጠየቅ ሰው ሁሉ፤እውነቱን ይናገር ፤-የሚናገር ቢኖር፤
ብርሃን ነው ጨለማ ሰውን የሚያሳፍር ?
ጨለማን ይጠላል ሰው ጨዋ ለመባል ፤
ብርሃን ሲያሸማቅቅ አያውቀው ይመስል !

ጨልም ! ጨልም ! ድፍን ብለህ ጨልም !
ዓይኖቻችን ይጥፉ ፤ አያዩም ፤ አይጠቅሙም ።
ውሾቹ ይጩሁ ፤ ጅቦቹ ያጉዋሩ ፤
የሌሊትም ወፎች በራስ ላይ ይዙሩ ፤
አራዊት ይንጫጩ ፤ አጋንንት ይጋጩ ፤
የብርሃንም ጨዎች በጣር ይወራጩ ፤
ዛሮችም ይጋልቡ ፈረሶቻቸውን ፤
ሁሉም ይኮላተፍ የዛር ፈረስ ይሁን ፤
ድብልቅልቁ ይውጣ ሰው ሰውን አይለካው ፤
የራሱን ሰውነት መጠኑን እስቲያውቀው ።

ጨልም ! ጨልም ! ድፍን ብለህ ጨልም !
ዓይኖቻችን ይጥፉ ፤ አያዩም ፤ አይጠቅሙም ።
ሰውረን ጨለማ አድነን ከብርሃን ፤
ምሥጢር እንዲጠበቅ ገበና እንዲሸፈን ፤
ብርሃኑ ይጨልም ! ጨለማውም ይድመቅ !
ጸሐይዋ ትሰበር ! ምሰሶዋ ይውደቅ !

ጨረቃዋ ትጥፋ ! ኮከቦች ይርገፉ !
ጨለማውን ለብሰው መሬት ይነጠፉ !
ሰማዩ ይቀደድ ! ይጣራ ፣ ዶፍ ይውረድ !
ይጥፋ የሚማገድ ፣ የነደደው ይብረድ !
ጨልም ! ጨልም !- ድፍን ብለህ ጨልም !
ዓይኖቻችን ይጥፉ ! አያዩም ፣ አይጠቅሙም ።
ለመጋለጥና ለማጋለጥ ብቻ ከጠቀመ ብርሃን ፣
ከነምቹ ይጥፉ ፣ አልበጀንም ጥመን ።
አይቶ የማይገምት ፣ ታይቶ የሚገመት ፣
የጨለማ ሰው ነው የቀን አሻንጉሊት !
አንዱ አንዱን ሳያውቀው በርግጥ እያወቀው ፣
አንዱ አንዱን ሳይንቀው ፣ በርግጥ እየናቀው ፣
በብርሃን ደግነት ፣ በጨለማ ክፋት ፣
ቁም ነገር የሌለው ዕለት በለት ስደት ።
ጨልም !- ጨልም !- ድፍን ብለህ ጨልም !
ዓይኖቻችን ይጥፉ ! አያዩም ፣ አይጠቅሙም ።
መንታ መንታውን ነው ጭካኔ እሚወልደው ፣
አንደኛው መከታው አንደኛው ጠሩ ነው ።
ንዴት በሌለበት ምን ማለት ነው ትዕግሥት ?
ፍርሃት በሌለበት አለ ወይ ጀግንነት ?
ክብርን የማያውቁ
እንዴት ውርደት ናቁ ?
ድህነት በመሬት ጭራሽ ባይፈጠር ፣
ጌትነት ምን በልቶ ይጠበድል ነበር ?

ጨልም ! ጨልም !- ድፍን ብለህ ጨልም !
ዓይኖቻችን ይጥፉ ! አያዩም ፣ አይጠቅሙም ።
ጨለማ አስረግዞ ጨለማ ሳይወልደው ፣
ብርሃን የት ይገኛል ጨለማ እሚገልጠው ?
ጨክን ጨለማችን ጭላንጭሉን አጥፋው !
ብርሃን ከኛ ይፍለቅ ፣ በውሉ ስንሻው ።
ውበት ስሙ ይጥፋ ፣ እኛ እስትንፈጥረው ፣
እውነት ያንቀላፋ እስትንቀሰቅሰው ።
በርታ ጨለማችን ፣ ተጨነቅ ! ተጠበብ !
እምጥና ውለድ ለቁም ነገር ጥበብ ።

ጨልም !- ጨልም !- ድፍን ብለህ ጨልም !
ዓይኖቻችን ይጥፉ ! አያዩም ፣ አይጠቅሙም ።
የግዜር ሕያው ትንፋሽ ካለ በውስጣችን ፣
አስረግዘን ብርሃን ጨለማው አውራችን ።
የተዳፈነውን በቀኑ ለኩሰው ፣
እሳት በሳት ነጥሮ እሳት እንዲሆን ሰው ።
ጨለማ ያስታርቀው የብርሃንን ጠላት ፣
ጨለማና ብርሃን ሰውን አይክፈሉት ።
በብርሃን ያየነው ሲጨልም ከጠፋ ፣
ይጨልም ጨርሶ ፡- ጨለማ ምን ከፋ !
ስብሐት ለጨለማ !- ይጨልም ! ይጨልም !
ዓይኖቻችን ይጥፉ ! አያዩም ፣ አይጠቅሙም ።

የጥንቱ አገረሽ

ሁሉን የሚችል ዳስ አንጣሎ ፤ ገትሮ ፤
ደልድሎ ፤ አሳምሮ ፤
ሊጡ ተቦካና እንጀራው ተጋግሮ
ለብሶ ተከምሮ ፤
ጠጁ ተጣለና በጠላ ጉሮሮ
ሊወርድ ተደርድሮ ፤
ወጡ በያይነቱ ባዋቂ ተሠርቶ ፤
ቁርጡ ተሰናድቶ ፤
ሰው ሁሉ ለመብላት ፤ ለመጠጣት ጓጉቶ ፤
ሲጠብቅ ሰንብቶ ፤
አዝማሪው ለዘፈን ቆሞ ተዘጋጅቶ ፤
ማሲንቆው ተቃኝቶ ፤
ጨዋታ ፈረሰ !
ዳቦ ተቆረሰ !
ሙሽራው ጠፋና ሠርጉ ተበላሸ ፤
የተጠራው ሸሸ ፤
ጊዜ ከዳውና በጊዜው ላመሸ ።
ዳሱ ተረበሸ ፤
የጥንቱ አገረሸ ።

ናፍቆት

በኔና አንቺ መሀል ወንዝ አለ መራራ ፤

አላገናኝ አለኝ ፤ ሆኖኝ ባላጋራ ፤

ያዘኝ ደሀነቴ ድልድይ እንዳልሠራ ፤

ዋኝቼ እንዳልመጣ ውሀ ልቤ ፈራ ።

አንቺ ወዲያ ማዶ ፤ እኔ ወዲህ ማዶ ፤

ልባችን በስሜት ርቀቱን ጥሶ ፤ ገደሉንም ንዶ ፤

ልዩነት ጅረትም ፈሶ ፤ ወርዶ ፤ ወርዶ ፤

ቀን ሳይሞላ አይቀርም ለኛ ተዋኅዶ ።

እስቲመቸኝ ድረስ ፤ እስቲ መችሽ ድረስ እስከዚያ ልጨነቅ ፤

እስቲመጣ ጊዜ ያንን ወንዝ የሚያደርቅ ፤

የስሜቴን ምሥጢር እስተዚያ ልደብቅ ፤

ያንን ፈገግታሽን እነዚያ ዓይኖችሽን በናፍቆት ልጠብቅ ።

ከልቤም አትወጪ!

ከልቤም አትወጪ!

አርፈሽ ተቀመጪ!

እኔ እንቺን መውደዴን እኔም አላዝበት፤እንችም አታገርበት፤

ጥሎሽ ነው ፤ ግዴታ ፤ ሥልጣንም የለበት ።

ጸሐይን ስትዞር መሬት ወዳ አይደለም ፤

ግዴታ ሆኖ ነው የምወድሽ እኔም

አንቺ ሰደድ እሳት ፤ እኔ የሳት እራት ፤

እንዴት ልከላከል የተፈጥሮ ምትሐት!

ውደጅኝ አልልም ፤

ሌላም አልጠይቅም ፤

እንከን አልይብሽ ፤

ክፉ አይድረስብሽ ፤

ለምልሚ በውበት ፤

አብቢ በኩራት ።

ከልቤም አትውጪ !

አርፈሽ ተቀመጪ!

ፍቅር መስዋዕት ሆነ

ያንቺ ጉሹ ፍቅር ከኔ ቅራሪ ጋር ፤

ቃር ይሆናል አሉሽ ? ሲያቅራቸው ይኑር !

ቅራሪም ጉሽ ነበር ፤ ጉሽም አይቀርለት ፤

ጥማት ለተሰማው የት ነበር ልዩነት ?

ጉሽና ቅራሪ ጠባዩ እሚለየው ፤

ስሜት በሌለበት በወረት ጊዜ ነው ፤

ድፍን ጽጌ ረዳ ፤

ጉሽ ፍቅርሽ ሰው ከዳ ፤

ጊዮርጊስ በፈረስ አልደረሰም በነፍስ ፤

ፍቅር መስዋዕት ሆነ እንዳለ በጥንስስ ።

የኔ ፍቅር

የኔ ፍቅር ላንቺ ከጉዳይ ባይገባም ፤
ብታውቂኝ ፤ ባታውቂኝ ፤ አንቺ ባትወጂኝም ፤—
ፍቅሬ አይለወጥም ፤
ለውጡን አልጠብቅም ፤
ስሜቴ አይሸጥም ።
የኔ ፍቅር ላንቺ ቢጠቅምም ፤ ባይጠቅምም ፤
ክብሬ ነው ብትዪ ፤ ውርደት ነው ብትዪም ፤—
ፍቅሬ አይለወጥም ፤
ለውጡን አልጠብቅም ፤
ስሜቴ አይሸጥም ።
የኔ ፍቅር ላንቺ ገንፍሎ ባይፈስም ፤
አበድሁኝ ፤ ሰከርሁኝ ፤ ታመምሁኝ ባልልም
ፍቅሬ አይለወጥም ፤
ለውጡን አልጠብቅም ፤
ስሜቴ አይሸጥም ።
የኔ ፍቅር ላንቺ የምኞት እንጕሎት ፤ ሽውታ አይደለም ፤
አግኝቼም አልጠግብሽ! አጥቼም አልከዳም! —
ፍቅሬ አይለወጥም ፤
ለውጡን አልጠብቅም ፤
ስሜቴ አይሸጥም ።

የሕይወት ቃር

ባንቺ ፤ በኔ ፍቅር ፤
በዓይንና ባፉ ሰው ሁሉ ሲናገር ፤
እኛ ሁለታችን እንሰቃይ ነበር ፤
እኛ በተዋደድን ጎረቤት ሲሸበር!
ነግሬሽ ነበረ ፤ ከንቱውን ምኞቴን ፤
የስሜቴን ቅዠት ላንቺ ስል መጥላቴን ፤
ሰው ሁሉ ጨርሰን ፤
እኔና አንቺ ቀርተን!
ቦርቀን ! ጨፍረን!
ሲደክመን ተኝተን ፤
እኔና አንቺ ብቻ ፤
በፍቅር ዘመቻ!
ከጎኔ ሳትወጪ ከጭቃ ሳልወጣ!
አዲስ ዘር በዘራን! — ሰው ከሰው የወጣ!
መትረየስ የለንም ፤ ጥይትም የለንም ፤
ሰውም አንጨርስ ለብቻም አንሆንም ፤
አዲስም ዘር አይኖር ፤ ያው ነው እንደጥንቱ ፤
ችግር የሞላበት ፤ በደሉ ጥቃቱ ።
የሰው ዓይን በላው ! የኔን ያንቺን ፍቅር!
ግዴታ ገባብን ፤ — ችግር የሕይወት ቃር!

እኔ ባንቺ አልፈርድም

እኔ በአንቺ አልፈርድም በጊዜው ነው እንጂ ፤
አትፍረጂ በኔ በጊዜው ፍረጂ ።
«ወደድሁህ» ወደድሁሽ ፤ » ብለን ተቃቅፈናል ፤
ስቀን ተጫውተናል ፤ አብረንም ሰክረናል ።
አዝነን አልቅሰናል ፤ አብረን ተጨንቀናል ፤
በጋና ክረምቱን አፈራርቀነዋል ።
እኔ በአንቺ አልፈርድም በጊዜው ነው እንጂ ፤
አትፍረጂ በኔ በጊዜው ፍረጂ ።
መስኮች ይናገሩ ጋራው ሸንተረሩ ፤
ይመስክር ዓየሩ ፤ ዛፎች እስቲ ያውሩ ፤
ኮከቦች ፤ ጨረቃ ወርደው ይመርመሩ ፤
ሰው ጠልተን ፤ ሰው ሸሽተን ፤ እነሱ ነበሩ ።
እኔ በአንቺ አልፈርድም በጊዜው ነው እንጂ
አትፍረጂ በኔ በጊዜው ፍረጂ ።
የክረምቱ ውሀ እንደበላው መሬት ፤
ጊዜ ልባችንን እየፋቀ አሻክሮት ፤
እየተጋጨብን ምኞትና ምኞት ፤
አቃተን ዳገቱ ፤ አጣን ብልሃት ፤ ብርታት ።
እኔ በአንቺ አልፈርድም በጊዜው ነው እንጂ ፤
አትፍረጂ በኔ በጊዜው ፍረጂ ።

—ዕፀ ፡፡ በለስ —

ተንቀሳቃሽ ፤ ውብት ፤ ሕይወት ያለው ውብት ፤
እንደነጐድጓድ ነሽ ፤ማዕበል ፤ ፋዋፋዋቴ ፤ ነበልባለ እሳት ፤
የዓይኖችሽ ጨረር፤ የጥርስሽ ውጋጋን ፤
ፈገግታሽ ጸዳል ፤የውበትሽ ሥልጣን ፤
ሳታውቂኝ ሳላውቅሽ ፤
በሩቁ ወደድሁሽ ፤
ወደድሁሽ! አጭር ቃል ፤
ላንቺ መች ይበቃል!
እንዳንቺ ብታደል በብቃት ብፈጠር ፤
ምኞት ተስፋ ነበር!
አንቺ ዕፀ - በለስ ፤
አንቺ ያይን ድግስ!
አልፎ አልፎ ስታደል ሳይሽ በጨረፍታ ፤
ግራ ይገባኛል ፤ ፈርቼ ይሉኝታ ፤
ያለድምፅ ያለቃል ፤
ቅብጥብጥ! ድንግርግር! —ሕፃን ልጅ ይመስል!
አልችልም ልቀርብሽ ፤
ዓይን ነው አጀብሽ!
ሌላ ምን ልበልሽ?
ዓይኔ ይከተልሽ!

ለማንም አትሆኝ ፤ አታገኝም አቻ ፤
የደስታ ሐዘን ፤ ዓይን ይብላሽ በዛቻ !
አንቺ ክልክል ፍሬ ፤
አልደርስብሽ ጥሬ ።

አንቺ ከሌላ ዛፍ እኔ ከሌላ ዛፍ እንዳልሆነ በቅለን ፤

ባሻገር ባሻገር እንተያያለን ።
ሳይሽ እኖራለሁ ፤
ብትወጂም ባትወጂም ቁራኛሽ ሆኛለሁ ።
መንፈስሽ ቢናወጥ ፤ ልብሽም ቢሰወር ፤
ስሜን ብትጠሪ በደብተራ ምሥጢር ፤
ቡዳ በላሽ ቢሉሽ ግራ የገባቸው ፤
ማርከሻ የሌለው ምኞት ነው በያቸው ።
ዓይን እምላክ እንዳለው ፤ ፍቅርም ካለው አምላክ ፤
የልቤን ይንገርሽ ፤ ገብርኤልን ይላክ ።

አንቺ ዕፀ — በለስ ፤

አንቺ ያይን ድግስ ።

ላንቺ እንዳላዋይሽ ሩቅ ነሽ ፤ ሩቅ ነሽ ፤
ለሰው እንዳላዋይ ትታሚብኛለሽ ፤
የልቤ ምሥጢር ነሽ ስምሽን አልጠራ ፤
ምኞት እንዳይጋጭ ከፋከራ ጋራ!

ይታመቅ ስሜቴ! ይታፈን ምኞቴ!
ይወሰን በልቤ እምሮቴ ፤ ናፍቆቴ ።
ብቻዬን ልጨነቅ አንቺ አትጨነቂ ፤
ሳቂ ፤ ሳቂ ፤ ሳቂ ፤ ተፍለቅለቂ ፤
ይቁለጭለጩ ዓይኖችሽ ዙሪያሽን ያድምቁት ፤
የበረደው ይሙቅ ፤ የጨለመው ይብራ ፤ የከፋው ይደሰት

አንቺ ዕፀ — በለስ ፤

እንዴት ብዬ ልድረስ!

ጽላት ልቅረጽልሽ ፤ ጣዖት አምላኪ ነው ይበሉኝ ግድ የለም፤
ላድንቅሽ !ላምልክሽ! ውዳሴሽን ልድገም ።
ሲከፋኝ ፤ ሲጨንቀኝ ፤ ክፉዎች ሲያስከፉኝ ፤
የኑሮዬ ትግል ቁልቁል ሲጎትቱኝ ፤
ዓይኔ ልቦናዬ ፤ ዕርገት አንቺ ሁኚኝ ።
የኔ ፤ ለእኔ አልልሽ ፤ የሕልም እንጀራ ነሽ ፤
እኔ ነኝ ምርኮኛሽ ፤
የኔ ፤ ለእኔ ፤ አትዪኝ ፤
አንድ ኢምንት ከብዙ ፤ አንቺ የማታውቂኝ ።
ባይሽ መቼ አነሰኝ!

አንቺ ዕፀ—በለስ ፤

አንች የውበት መቅደስ ።

—አስናቀች—

ስወዳት ፤ ሳልነግራት ፤
ሳከብራት ስፈራት ፤
ሳታውቅ የኔ ንግሥት ፤
ለጋ ፍጹም ውበት ።
ሳይታሰብ ድንገት ፤
በቃት ።
ፈገግታዋን ሳላይ ድምፅዋንም ሳልሰማ ፤
መርዶዋ ደረሰኝ ፤ የቃኤሉ ድንጋይ አድርጓት ኢላማ ።
ያኔም አልቀረብሁአት ፤
አሁንም አልራቅሁአት ።
ሳስቼ ፤ ሰስቼ ፤
ራሴን ጎድቼ ፤
የማይሆነው ሆነ የሚሆነው ቀረ ፤
የሞተው ገደለ ፤ ኃይል ተሰወረ ።
የሕይወት ምሥጢሩ ፤
ጣጣው ፤ ግርግሩ ፤
ፍርሃቱ ፤ ሥጋቱ ፤
ጥቃቱ ትዕግሥቱ ።
አለኝታና ተስፋው ፤
ፍቅርና ውለታው ፤
ያልፋል በዝምታ ፤
በዕንባ ጠብታ ፤
አስቀያሚ ጥይት በድን ደደብ መልእክት ፤
ዓይን የማትችል ልጅ ደረሰች ለጥይት ።
ያቺ ለጋ ወጣት በዝምታ አለፈች ።
ዝም አለች፤ ውበትዋን፤ ድምቀትዋን ኃይልዋንም ሰወረች ።
ሐዘንም ቅሬታም ትዝታም አስናቀች ።

ባልተመቸ ጊዜ

ባልተመቸ ጊዜ ፤ ባልተመቸ ቦታ ፤
የክረምት ጸሐይ ፤ የሌሊት ብልጭታ ፤
ከመ ቅጽበት ታይታ ፤
ለዛ ባለው ውበት ፤ በሕፃን ፈገግታ ፤
እንዲያው በቀስታ ፤ እንዲያው በችልታ ፤
በማታውቀው ኃይልዋ ልቤ ውስጥ ገብታ ፤
ያረፈች ፤ የተኛች ፤ ድብቅ ነፍስ ነክታ ፤
እንቀሳቀሰችኝ ነቃሁኝ ባንድ አፍታ ።
ባልተመቸ ጊዜ ባልተመቸ ቦታ ፤
የክረምት ጸሐይ የሌሊት ብልጭታ ።
በማላውቀው ሕይወት በማላውቀው ምልዓት በተስፋ በደስታ
ሳታውቅ ነከረችኝ ። አየች ስንገላታ ።
ቁም ነገሩን ሁሉ አድርጋው ጨዋታ ፤
እሷ ተደበቀች ። በርዋን በኔ ዘግታ ።

ወይአልወደደችኝወይምአልጠላችኝመውደድመጥላትፈርታ

መንፈሴን ጨነቀው በስሜት ግዴታ ።

ባልተመች ጊዜ ባልተመቸ ቦታ ፤

የክረምት ጸሐይ የሌሊት ብልጭታ ።

ኃይልዋን አሳይታ ፤

ራቀች ፤ ረቀቀች ፤ ሳይንስ የት ተገኝታ!

እውን የነበረችው የደህ ሕልም ሆነችምኞትን ተከታ፤

የሕይወት ጠባሳ ሆናለች ትዝታ ።

ፍቅር በግዴታ በኑሮ ተረታ ።

ከኔ ጋር የቀረው ውልታ! ቅሬታ!

ባልተመቸ ጊዜ ፤ ባልተመቸ ቦታ ፤

የክረምት ጸሐይ የሌሊት ብልጭታ ።

ይናፍቀኛል

ትዝ ይለኛል ፤
ይናፍቀኛል ።
ቀልድና ጨዋታው ፤
ዘፈኑ ጭፈራው ፤
አሉባልታው ፤- ወሬና ሐሜቱ ፤
ፍርሐቱ ፤ ስጋቱ ፤
ችግሩ፤ በደሉ ፤
የእድገት ክልሉ ፤
ትዝ ይለኛል ፤
ይናፍቀኛል ፤
ሳርና ቅጠሉ ፤
ተራራው ፤ ገደሉ ፤
ወንዙ ሸንተረሩ ፤
ዝናቡና ዓየሩ ፤
አቧራና ጭቃው ፤
እበቱ ፤ ፋንድያው ፤
ትዝ ይለኛል ፤
ይናፍቀኛል ።

፲፱፻፳፯ ዓ፡ ም፡

ሕያው ኢትዮጵያ ።

ሌሊቱ ሲነጋ ፤ ጨለማው ሲወገድ ፤ —
በፈጠርነው ብርሃን እያየን ስንሄድ ፤ —
ደመናው ሲገፈፍ ፤ ሰማዩ ሲጠራ ፤ —

የተኛው ሲነቃ እየተንጠራራ ፤ —
ይንጠጠራ ሁሉም! ሰማዩን ፤ ይቡዋጠው!

የእውቀትን ምሥጢር ኃይሉን እንዲገልጠው ፤
ሀሳብና ሀሳብ ይፋጩ ፤ ይጋጩ ፤

በውል ፤ በቁም ነገር ፤ በጋራ እስቲቋጩ ።
ሕያው ኢትዮጵያ ትለምልም በኅብረት!
አረሙ ይነቀል ! ይቅር ስጋት ፍርሃት!

ወንዱ ልጅ ያቅራራ! ይፎክር! ያስመስክር!
ጠላት መግቢያ ይጣ! ይሸበር! ይደንብር!
ወንዱ ደሙ ይፍላ! ይቆጣ! ይገንፍል · ስሩ እስቲግተረተር!
በነፃነት ፍቅር ፤ ለራሱ ባለው ክብር ፤
ክንዱን እያነሣ አሻፈረኝ ብሎ ፤ ጥቃትን ይጋተር!
የከፋው ይከፋ የደላው አይተኛ በቅዠት ይሸበር!
እንዳይጥ መሽቆጥቆጥ አንገት ደፍቶ መኖር
ወንድነት አይደለም ፤ ክብርን ሽጦ ማደር ።
ሕያው ኢትዮጵያ ትለምልም በኅብረት!
አረሙ ይነቀል! ይቅር ስጋት ፍርሃት!

የሴቲቱ ውበት ፤ ጸጋ የደም ግባት ፤
ጠባይዋ ፤ ምግባርዋና ፍቅርዋ እንደሚስት እንደናት ፤
ያዉደው አገሩን ፤ ዓየሩን በኩራት !

ይታፈር ሴትነት ! ይከበር ሴትነት !
ሴት ትኩራ በወንዱ ፤ ወንዱም ያኩራ በሴት
የወንዱን አልሜ ያንን የጨው ጭንት ፤
እምቢ ትበለው ሴት ! በሴት አይጫወት
ሴት የሌለው አገር ወንድም አይበቅልበት !
    ሕያው ኢትዮጵያ ትለምልም በኅብረት !
    አረሙ ይነቀል ! ይቅር ስጋት ፤ ፍርሃት !
ከበሮው ይደለቅ ! ሰው ይነቃነቅ !
ሕፃኑ ይቦርቅ አዋቂው ይፈንድቅ
ሀብታም ካለም ይጥፋ ! ደሀም ካለም ይጥፋ !
የሰው እኩልነት ይታወጅ በይፋ !
የፍካሬ የሱስ ትንቢቱ ይፈጸም ፤
ጠማማ ጠማማው ይቃና ይታረም !
እምቢልታው ይነፋ ! ይምጣ ! ምጽዓት ይምጣ !
ጽድቅና ኃጢአቱ ተገልጦ እንዲወጣ ።
    ሕያው ኢትዮጵያ ትለምልም በኅብረት!
    አረሙ ይነቀል ! ይቅር ስጋት ፍርሃት !
ፏፏቴው ይንከትከት ! ይንጎድጎድ ! ይዥጎድጎድ !
            እያጉዋራ ይውረድ !
ይውረድ ቆላው ይርካ ! ይውረድ ቆላው ይብረድ!
ወፎቹ ያፏጩ ! ጠግበው ይዘምሩ !
የንሱን እልልታ ያስተጋባ ዓየሩ!
ሰማያዊ ይሁን ሰማዩ ይጥራና ፤
ጸሐይዋን እያግድ ጥላሸት ደመና !
መሬትዋ ትለምልም ! ትድመቅ በቀለሞች !
መዓዛና ጣዕምዋ ያውጁ ምሥራች!